# የዓለም አቀፉ ሰልፍ ድራማ ግምገማ

በጄንዋሪ 14 ሰላማዊ ሰልፍ ብርቱካን ሜዴቅሳ እንድትፈታ በሚል ደጋፊዎችዋ ሳይ ታች ሲሉ ከርመው በዲሲ መቶ ሺህ ያህል ሰው ይወጣል በተባለበት ከተማ ከሁለት መቶ ሰልፈኛ አለመብለጡ አስተባባሪዎቹ ትልቅ አሻጥር ሰርተዋል ወይም መቶ ሺ ምን ያህል እንደሆነ የማያውቁና ግምት የሌላቸው ናቸው ያስብላል። እኔ ግን ሰልፉን ያስተባበሩት ሰዎች ከኋላ ሌላ አጀንዳ በመያዛቸው ሕዝብ አልተሳተፈበትም እላለሁ። እንዲያውም አንድ የዲሲ ነዋሪ የሆኑ ሰው በአንድ መጣጥፋቸው ሳይ ይህንኑ አስመልክቶ በጥቂቱ ገልጸውታል። እኔ የዋሽንግተን ዲሲ ነዋሪ ስላልሆንኩ ከማውቃቸው ሰዎች ምን ያህል ሰው እንደወጣ ሰማሁ እንጂ ብዛቱን አላየሁትም።

ሌላው ይቅር ምነዋ ታዲያ በእኛው ከተማ በቦስተን ያውም እነ አቡጊዳና የብርቱካን ድርጅት ሲቀመንበር ባለበት፣ በሎስ አንጄለስ፣ በኒዮርክ፣በላስ ቬጋስ እና ሌሎችም ከተሞች ሰልፍ አልተዘጋጀ? ምነዋ ጎረቤት አገር በካናዳ ትላልቅ ከተሞች በኦታዋ፣ በቶሮንቶ፣ ካልጋሪ፣ ዊኒፔግ፣ ኩቤክ ወፍ ጭጭም አላለ? ሲያትል አጠገብ በመኖራቸው የብርቱካንና የብርሃኑ ሰዎች ከቫንኮቨር ጥቂት ሆነው ወደ ሲያትል እንደሄዱ ሰምተናል በከተማቸው ለማድረግስ ምን ተሳናቸው? ምናልባት ቁጥራቸው 10 ስለማይሞላ ይሆን? በአውሮፓ ስዊዘርላንድ፣ ስዊድን እና ለንደን በመቶዎች የሚቆጠሩ ሲወጡ አንዳንድ ከተሞች አስራ ሰባት፣ ሃያ እና ሰላሳ የማይበልጡ ታይተዋል። በአፍሪካ፣ በካናዳ፣ በኤዥያ፣ በአውስትራሊያ ምንም ሰልፍ ካልተደረገ ዓለም አቀፍ የሚባለው ነገር እንዴት ነው? በአጠቃላይ "በዓለም አቀፉ ሰልፍ" በሁሉም ከተሞች የወጣው ሰለፈኛ አንድ ሺህ ሰው ያህል እንኳን አልሞላም። በእርግጥ ድምጽ ለማሰማትና ለመጮኽ አንድም ጥቂትም ሰዎች ቢወጡ ዓላማው ነው እንጂ ብዛቱ ዋጋም የለው። አዎን ወያኔን ማውገዝና የታሰሩት ይፈቱ ከሚለው ትግል አንጻር የተደረገው ሰላማዊ ትግል ይደገፋል። ትግላችን ግን፣ ዓላማችን ግን ለአንድ ቀን ሰልፍ አደረግን ብለን ለድርጅታችን ስምና ዝና ለመግዢያና ድል የተደረገ ይመስል ለመፎከሪያ ሳይሆን፣ የተዳከመውን ትግል አፋፍመን እውነተኛ ለውጥ የሚመጣበትን መንገድ ተጉዘን የወያኔ ዘረኛና አምባገነን አገዛዝ ተወግዶ የሕዝብ መንግሥት እስኪመሰረት ድረስ ለመግፋት ነው መሆን ያለበት። የጄንዋሪ 14ቱ ግን ከጀርባው መልዕክት ያለው የተቀነባበረ የተንኮለኞች ግርግር ነው።

ከሰለፈኛው መካከል ለእውነት በሀገር ፍቅር ስሜት ተቃጥለው የወጡ ሰዎች ሲኖሩ እንደሚችሉ ምንም ጥርጥር የለውም። የሰልፉ አስተባባሪዎች እና ሰልፉን እንዲካሄድ መመሪያ የሰጡት ሳይ ግን ያስጥርጥር አነማን መሆናቸውን ተደርሶበታል። ዳግም ተታለን አብረን የምንነዳ ከብቶች ወይም ጅሎች አለመሆናችንን ግን ሲያውቁት ይገባል። እውነተኛው የትግሉ ድጋፍ አካሎች ወይም የአንድነት ኃይል ክፍሎች ከሕዝባችን ፍላጎትና እንቅስቃሴ ጋር የተዋሃደ፣ የተሳሰረ ትግላቸውን አጠናክረው እንደሚያካሂዱና የወያኔን ግብዓተ መሬት ቀን እንደሚያፋጥኑት በእርግጠኛነት መናገር ይቻላል።

ትግሉን የገደሉ፣ ደጋፊውን የከፋፈሉ፣ የሕዝብን አደራ በልተው አውሮፓና አሜሪካ ከድተው የቀሩት፣ በፍርሃትና በጥቅም የተገዙት ሰዎች ግን በቅንጅት ዝናና ስም ትግሉን እንምራ ሲሉን በጠበላችሁ ማለትና ማነነታቸውን ማጋለጥ፣ ትግሉን መምራት አይችሉምና

ዞር በሉ ልንላቸው ይገባል፡፡ የሕዝብን ሰላማዊ አመጽ ያከሸፉ ጦር መርተን ከአስመራ ተነስተን በ6 ወር ውስጥ ነጻ እናወጣችኋለን ሲሉን መጀመሪያ እራሳችሁን ከሆዳችሁና ከሥልጣን፣ ከፍርሃትና ከአድርባይነት ነጻ አውጡ ልንላቸው ይገባል፡፡ ከኢሕአፓ ተገንጥለው በአንጃኛነት የተሰለፉትን ከወያኔ የሚደባለቁበት ቀን ረዝሞባቸው ያንን ለማፋጠን "እኛ እንምራችሁ" ሲሉን ወጊዱ ልንላቸው ይገባል፡፡ የ18 ዓመት ዘረኝነት አገዛዝ ያንገሸገሸውና ከዘረኝነት አገዛዝ መቼ ተላቅቄ አያለ የሚታገለውን ሕዝብ፣ ዓረና ትግራይ ብለው እነ ገብሩ አሥራት እነ ሰዬ አብርሃ ሲነሱ መጀመሪያ ለሕዝብ ፍርድ ቀረቡ ማለት መቻል አለብን፡፡ እነዚህ ናቸው ዛሬ ትግሉን እንምራ የሚሉን፡፡ የሲቪሲቲ ፓልቶክ ክፍል እና የትግራይ ተወላጆች የብርቱካን መታሰር አንገብግቧቸው "ብርቱካን ትፈታ ትፈታ መሪያችን እርሷ ነች" ሲሉን ኸረ ነገሩ ምንድነው? ብለን መጠርጠር አለብን፡፡ ያልጠረጠረ ተመነጠረ ተብሎ የለ፡፡

ኢትዮጵያ ወስጥ መችም ሕዝብ ሀሳቡን የመግለጽ ነጻነት ባይኖረውም ነጻ ጋዜጣ፣ ሬዲዮም ሆነ ቴሌቭዥን ባይኖረውም በቤቱና በትግሉ መስክ የራሱን ስራ እየሰራና ትግሉን እያካሄደ ይንዛል እንጂ የሰሞኑ የአውሮፓና የአሜሪካ የሰልፍ ግርግርና አጀንዳ ጉዳዬም ብሎ ያጤነው የለም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ እኮ የሚጠቅመውን የራሱን የሆነውን ክፍል ጠንቅቆ ያውቃልና አሜሪካና አውሮፓ ያሉት የኮንግረስ አባላት ወይም ፓርላሚንቴሪያንስ ሳይሆኑ ወሳኙ ራሱ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆኑን ስለሚያወቅ ጊዜው ሲደረስ የሚፈልገውን ያደርጋል፡፡ የውጭው ድጋፍ አካልም የሕዝቡን የልብ ትርታ እያዳመጠ ትግሉን በሚችለው አቅምና መንገድ ያካሄዳል ይደግፋል፡፡

የውሸትና የሴስ ጦር ሰባቂዎች፣ ኢትዮጵያን ለማጥፋት የተነሱ ጦረኞች "ነጻ ያወጡሃል" ባዮች፣ እኛስ ከማን እናንሳለን ባይ ሥልጣን ናፋቂ አንጃዎች፣ የወያኔ እድሜ ቀጣዮች፣ በሆዳቸውና በጥቅም የተገዙ አስመሳይና አጀንዳ ነጣቀዎች እናካሂዳለን ብለው በውጭው ዓለም የሚወራጩት እንኳንስ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለራሳቸውም የማይሆኑ ከንቱዎች ናቸው፡፡ ኢትዮጵያን ለመበታተን በውጭ ኃይሎች የተፈረደብንን ፍርድ ለማሳካት የሚራወጡ የውስጥ ጠላቶች፣ ከሃዲ ሆዳምና ባንዳዎች በመሆናቸው ታሪክም ሕዝብም ሲኮንናቸውና ሲፈርድባቸው ይኖራል፡፡ የዚህ ዩንቨርስቲ አስተማሪ ፕሮፌሰር እከሌ፣ የታወቀ ጠበቃ፣ ምሁርና የሃይማኖር መሪ በሚለው ከስማቸው በፊት በሚደረደረው የማዕረግ ስም መታለል የለብንም፡፡ ያስተማራቸውን ህዝብ የከዱ ምሁራን ናቸውና እነርሱን መናገር ኃጢያትና ወንጀል ሆኖ አፋችንን ሸብበን መቀመጥና አገራችን ስትጠፋ መመልከት የለብንም፡፡

ወያኔ የሚያወጣልንን አጀንዳ ይዘን እንደ ላሜ ቦራ መነዳት የለብንም ወይንም ጸረ ወያኔ መስለው የወያኔን ዕድሜ በሌላ መልክ ለመቀጠል የሚያጎነብሱት በታታኞች ተባባሪና ደጋፊ መሆን የለብንምና ትግሉን በጥራትና በብቃት ለመምራት ከሚችሉ ኃይሎች ጋር እንሰለፍ፡፡

ኢትዮጵያ በእውነተኛ ልጆችዋ ትግል ተጠብቃ ለዘለዓለም ትኖራለች!
የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሸንፋል!

ከወንዱ አሰፋ / ቦስተን፡ ማሳቹሴትስ /